# ሞትን አትውቀሱት

ሞትን አትውቀሱት - ሙት የሚከተውን፣
ገዳይ ሲገልለት - የሚቀበለውን፣
አህያውን ፈርቶ - ዳውላ ሆነና፣
ሞትን እንወቅሳለን - ዛሬም እንደገና።

የሚወዷትን ልጅ - ፅጌረዳ መሳይ፣
ቀምቶ ሲወስዳት - ዳግም እንዳታትይ፣
ወንድምዎ ሲሞት - አብሮ አደግ ሲለይም፣
ከቶ ላይተያይ - ላይነሳ ዳግም፣
አባት እናት ሲሞት - ሲገባ መቃብር፣
ትናንት ህያው አካል - ዛሬም እንዳልነበር፣
ሞትን አትውቀሱት - አትፈፅሙ ስህተት፣
እርሱ ተቀበለ - ሌላው ገደለለት።

ሰውን ሰው ይገድላል - መኖርን ከልክሎ፣
ሞትም ይከተዋል - ከእርሱ ተቀብሎ፣
በሽታ ይገድላል - ወይንም አደጋ፣
በር ከፋች ሌላ- ሞትም የሚዘጋ።

“ሀ” ብሎ ህይወትን - “አልፋ” ብሎ ኑሮ፣
“ፐ” ሞትም “ዖሜጋ” - ትናንትም ዘንድሮ፣
አንድ ነው አንድ ዓይነት - ከዓዳም ልጅ ጀምሮ፣
ግና ሰው ግብዙ - ሰው በሰው ፈራጁ፣
ሞትን ይወቅሰዋል - ሁሉም በየፈርጁ::

አምሳያውን ባይገድል - ባያሳድደው፣
በሽታን ቢያጠፋ - ቢተጋገዘው፣
ሞት በየት አድርጎ - ይወስዳል ሰው።

ምን አጠፋና ሞት - ሟችን በከተተ፣
ሰው ገዳይ ነው እንጅ - ሰው መግደል የሻተ፣
አትውቀሱት ሞትን - ሙት በሰበሰበ፣
ሞት ምን አቅም አለው - ሰው ለስው ካሰበ።

ዳግማዊ ዳዊት: ነሐሴ 2001 ዓ.ም.
ethio_dagmawi@yahoo.com